ኧረ የመሪ ያለህ!

የኢትዮጵያ አምላክ የድሮው የጥንቱ
በመከራዋ ቀን የደረሰክላቱ
ዛሬም እንደገና እጇን ስትዘረጋ
ከሚያንዣብብባት ውስብስብ አደጋ
መሰስ አርገህ አውጣት በምታውቀው ዘዴ
ከሥራት፣ ከፈና፣ ከጦር ከጎራዴ።
አንተን ተስፋ አድርጋ አንተኑ ተማምና
በመቅደስ በመስጊድ ጧት ማታ ለምና
ወደአንተ ስትመጣ ርዳታ ፈልጋ
ያዘት እንደ ድሮው እጇን ስትዘረጋ።
ኧረ እባክህ አምላክ እባክህ ፈጣሪ
በሥርዓት በፍትህ ሕዝብ አስተዳደሪ
የወገኑን ችግር ተካፋይ ተጋሪ
ስጣት ለኢትዮጵያ እውነተኛ መሪ።
ውሀ ቀጥኗል ብሎ ቶሎ የማያኮርፍ
አይቶ የሚታገስ ሰምቶ የሚያሳልፍ
ለወገን የሚያስብ ልበ–ሰፊ መሪ
ስጣት ለኢትዮጵያ እባክህ ፈጣሪ።
ጉልቻ ቢቀየር ወጥ አይጣፍጥምና
ከዘንድሮው ስህተት ከምናው ከታች እምና
ትምህርት የተማረ መሪ ስጠውና
ሕዝቡ ይገላገል ከሥራት ከፈና።
ትንንሹ ነገር እየተጋነነ
እንደተለመደው እንደ እምናው ከሆነ
ወይም እንዳለፈው ወይ ካለፈው ብሶ
በሽታው ከመጣ መልሶ መላልሶ
ምን እንሽር ብለን ነው የምንጠጣው ኩሶ?
ዲሞክራሲ ፍትህ በአገር እንዲሰፋፋ
ሕዝብ እንዲተባብር በፍቅር በተስፋ
ተከታይ አይደለም መሪ ነው የጠፋ።
እሱ ያወጣውን ሕግ የማያከብር
ተባብሮ እማይሠራ በንድ ድርጅ ሥር
እንዴት አድርጎ ነው ሕዝብ የሚያስተዳድር?
እኔ ያልኩት ይሁን ሌላው ገደል ይግባ
በማለት ለመጥለፍ አንዱ አንዱን ሲያደባ
ማየትና መስማት ያሳዝናል በጣም
አገር የሚያስቀድም እንዴት መሪ አይመጣም?
ለወገን የሚያስብ እንዴት መሪ አይመጣም?

ኧረ የመሪ ያለህ!!

ለፍትህ ለውነት ለነጻነት ብሎ
የቅንጅትን ቃል ጥሪ ተከትሎ
ያ ሁሉ ሰው ሞቶ ያ ሁሉ ሰው ቆስሎ
ያ ሁሉ ሰው ታሥሮ ስንቱ ተፈናቅሎ
ያ ሁሉ መስዋዕት አይከፍሉ ተከፍሎ
ባለመደማመጥ ባለመከባበር
ባለመስተዋዋል ባለመተባበር
በየምክንያቱ ሲጯጯህ ሲናቆር
የወገናችን ደም እንዴት መና ይቅር?
መቻቻል ሳይማር አንዱ ከአንዱ ጋራ
ባግባብ ሳይወጣ የሕዝቡን አደራ
ራሱ በወጣው በሕጉ ሳይሠራ
ደንቡን ተከትሎ ድርጅት ሳይመራ
ዲሞክራሲ! እያለ ሽህ ጊዜ ቢያወራ
አቤት የሚል የለም እንዲህ በቀላሉ
ድስኩርና ምግባር ሳይስተካከሉ።
ኧረ ልብ ሰጠን እንደ አለት ጠንክራ
ለወገን ለሀገር አብረን እንድሠራ።
ኧረ የመሪ ያለህ!!
በፍርሀት በጭንቀት ሁሌ መባነኑ
መታሰር፣ መገረፍ፣ መሞት፣ መታፈኑ
ወገኑን ወገኑ እንደ አውሬ ማደኑ
በልቾቱናልና መሰደድ ማዘኑ
እኛንም ለውጠን ልክ እንደዘመኑ።
በሀሳብ በተግባር መለያየታችን
ጠላት ከደረገን እርስ-በራሳችን
በሰላም ከልፈታን እምብኟሮ ችግር
ዲሞክራሲ ፍትህ እያልን መደናቆር
ምን ትርጉም ይሰጣል እስቲ እንነጋገር?
እንዴት አንማርም ከታሪክ ካለፈው
ኧረ በቃ! እያለ ከሚለፈልፈው?
እንዴት አንማርም ከታሪክ ካለፈው
ተባበሩ! እያለ ከሚለፈልፈው?

ኧረ የመሪ ያለህ!!

በተፈጥሮ በድርቅ እየተመከኘ
በእየሩ በእፈሩ እየተመከኘ
የኢትዮጵያ ችግር ሰው ሆኖ ተገኘ።
ያውም የማይማር ከታሪክ ካለፈው
ተባበሩ! እያለ ከሚለፈልፈው።
ከጥፋት ላይ ጥፋት ከበደል ላይ በደል
ለማንም የማይበጅ ተያይዞ ገደል
መሆኑን ተረድተን እንድንተባበር
በዚህ አዲስ ዘመን በዚህ አዲስ ጅምር

አዲስ መንፈስ ሰጠን አባክህ እግዚአብሔር።
በቃን መገዳደል በቃን ጦርነት
በቃን መጠላለፍ በቃን እሥራት
በቃን መሰያየት በቃን ድህነት
የወገን እንባ አባሽ ፍትህ አስከባሪ
አዲስ ምዕራፍ ከፋች አገር ወገን አኩሪ
ሰጣት ለኢትዮጵያ እውነተኛ መሪ።
የሰው ልጅ የሚኖር ነውና በተስፋ
ሕይወትና ንብረት በከንቱ ሳይጠፋ
ሰላም ብልጽግና በኢትዮጵያ ተስፋፍቶ
የሰው እጅ ማየት መሰመኑ ቀርቶ
ሕዝባችን አልፎለት በእሱነቱ ኩርቶ
እስከምናይ ድረስ ቸኩለናል በጣም
ሕልማችን እውን አርገው አምላክ ዘዴ አታጣም።
ለአጥፊ ልብ ሰጥቶት ስህተቱን አርሞ
የሕዝብን አደራ በግባብ ተሸክሞ
እንከ ስላንትያ በምንትያ ቀርቶ
ሲነግሩት ሲመክሩት እሽ ብሎ ሰምቶ
መሪና ተመሪ በዓላማ ተስማምቶ
ሰላም እርቅ ሰፍኖ አገር ተረጋግቶ
እስከምናይ ድረስ ቸኩለናል በጣም
ሕልማችን እውን አርገው አምላክ ዘዴ አታጣም።
የሕዝቡን ፍላጎት የልቡን ትርታ
ውስብስብ ችግሩን በዘዴ እሚፈታ
የሚገዛው ሳይሆን የሚያስተዳድረው
ከተፍ የሚልለት ሲያጣ ሲቸግረው
በምታውቀው ዘዴ በምታውቀው ታዕምር
መሪ ፍጠርለት አባክህ እግዚአብሔር።
የወገኑን ችግር ብሶቱን አዋቂ
ከወገን ጋር አልቃሽ ከወገን ጋር ሳቂ
ክፉውን በጎውን ተካፋይ ተጋሪ
ስጠው ለኢትዮጵያ ሕዝብ እውነተኛ መሪ።
ብርቱና ደካማ እኩል ፍርድ አግኝቶ
ሁሉም በሕግ አምኖ ለሕግ ተገዝቶ
እስከምናይ ድረስ ቸኩለናል በጣም
ሕልማችን እውን አርገው አምላክ ዘዴ አታጣም።
ኢትዮጵያ እናታችን ዛሬ እምታምጠው
ከማህጸን ከሆድዋ የሚገላበጠው
በሰላም ተወልዶ እሷም ተገላግላ
ከጣር ከጭንቀቷ አፎይ! አፎይ ብላ
እስከምናይ ድረስ ቸኩለናል በጣም
ሕልማችን እውን አርገው እግዜር ዘዴ አታጣም።
ለሥልጣን ለጥቅም እየተናከሰ
ራሱ ያወጣውን ሕግ እያፈረሰ
በታሪክ በትውልድ እየተወቀሰ

እስከመቸ ድረስ እንዲህ ይኖራል ሰው
ይሉኝታ ሳይገታው ሕሊናው ሳይወቅሰው?
ነጻነት ከሌለ ከሥራት ካፈና
ሰው ወጥቶ ካልገባ በሰላም በጤና
እድገት ብልጽግና አይገኝምና፣
አምላክ ልብ ሰጠን ከብረት የጸና።
የተፈጸመውን ዛሬና ትናንት
ስንመራመረው ስንመለከት
የመሪዎቻችን ሥራና ሕይወት
እጅግ ያስገርማል ያሳዝናል በጣም
ሕግ አክብሮ አዳሪ እንዴት መሪ አይመጣም?
ወገን እንዳያዝን ታሪክ እንዳይወቅሰው
እንዴት ያወጣውን ሕግ አይጠብቅም ሰው?

ኧረ የመሪ ያለህ!!

ኧረ እባክህ አምላክ እባክህ ፈጣሪ
ለሕዝብ የሚራራ አገር ወገን አኩሪ
ስጣት ለኢትዮጵያ እውነተኛ መሪ!
እንደውሀ እሚጎርፈው የሕዝቡ እንባ ደርቆ
ፍትህ ተስተካክሎ መብት ተጠብቆ፣
አንዱ ካንዱ ሳይበልጥ አንዱ ካንዱ ሳያንስ
አንዱ አንዱን ሳይገድለው ደም ሳይመላለስ
በወላጅ ጥፋት ልጅ ሳይወቀስ፣
ሙስሊም ክርስቲያኑ ጸሎቱ ተሰምቶ
በዘር መከፋፈል ወገዳደል ቀርቶ
ሁሉም በታሪኩ በህገኑ ከርቶ
እስከምናይ ድረስ ቸኩለናል በጣም
ሕልማችን እውን አርገው እግዜር ዘዴ አታጣም።
እኔ ሞኝ አንተ ሞኝ ሁለት ሞኝ አግኝተው
አለሁልህ ብለው ምለው ተገዝተው
እንደ ተልባ ስፍር እንደሙልጭልጩ
ሾርተት ሾርተት ሲሉ ሲጣሉ ሲጋጩ
በሥልጣን ሽኩቻ ወይ ባለመግባባም
ሲናቆሩ ማየት ያሳዝናል በጣም።
ሥልጣን አደራ ነው ከሕዝብ የተሰጠ
ደግም የማይገኝ አንዴ ከመለጠ
ብሎ እሚያስጠነቅቅ ወይም እማካሪ
ስጣቸው ለመሪዎች እባክህ ፈጣሪ።
ለቆሰለውና ለሞተው ብላችሁ
ለታፈነውና ለሥረኛው ብላችሁ
በቁፍ ለሚኖረው ለሕዝቡ ብላችሁ
ለተፈናቀለው ለወገን ብላችሁ
ኧረ ተባበሩ ስለፈጠራችሁ!
የተከፋፈለ ያልተባበረ ሰው

እየነጣጠለ ጠላት ሲደቁሰው
ሲገዛው ይኖራል ሲሰራው ሲያፈርሰው።
እንዴት እንማርም ከታሪክ ካለፈው
ተባበሩ እያለ ከሚለፈልፈው?
ጉልበታም በተራ ሥልጣን ተቀባብሎ
እስከ ልጅ ልጆችህ ረግጦ እንከበሎ
ቅጥ ቅጥ!! አርጎ ይግዛህ አፍኖ ከፋፍሎ፤
ምንም ብትበደል ምንም ብትጠቃ
እንቅልፍ ይጣልብህ ቶሎ እማያነቃ፤
ሌሊቱን ያርዝመው አይንጋልህ ቀኑ
ብሎ የረገመን ማነው ለመሆኑ?
ጧት የተቋጠረው ማታ እየተፈታ
ብትንትን ብትንትን የሚያደርግ በሽታ
ከቶ ከየት መጣ ከየትኛው ቦታ?
እውነት አይምሰልህ ልንገርህ ወገኔ
መለያየት ሞት ነው ለአንተም ሆነ ለእኔ።
ሕዝብ ከተባበረ መብቱን ካወቀው
የሚገፋው የለም የሚነቀንቀው።
ድር እንኳን ቀጭኑ ድር እንኳን ለሰላሰው
ሲያብር ሲተባበር ይበልጣል ከንበሳው
ማን አለብኝ ብሎ ጠግቦ ከሚያገሳው።
ያ ሁሉ! መስዋዕት ሰላም ካላመጣ
ይኸ ሁሉ! ጩኸት ሰሚ ጆሮ ካጣ
እንዲህ ብሎ ብሎ እንዴ ከፈነዳ
ወይ መውጫ! ወይ መውጫ! ወይ መውጫ ቀዳዳ
የሚያስኝ ይሆናል የሚመጣው እዳ።
ለሥልጣን ለገንዘብ ብቻውን ሮጦ
በፉ በጉልበቱ አንዱ አንዱን ዘርጥጦ
ያለተቀናቃኝ ሥልጣን ተቆናጥጦ
እንደ ተለመደው ሊገዛ ቀጥቅጦ
የሚያባብለንን የሥልጣን ጥመኛ
ከእንግዲህ በቀቶናል አንፈልግም እኛ!
ጥቅሙን አስቀድሞ አገር የማይጎዳ
ለሥልጣን ለክብር የማይከዳዳ
ለወገን አሳቢ ለአገር ተቆርቋሪ
ቃል–ኪዳንን ጠባቂ ተስፋውን አክባሪ
በሰላም በፍትህ ሕዝብ አስተባባሪ
ስጣት ለኢትዮጵያ እውነተኛ መሪ።
እግዜር ቢሉህ አቤት አላህ ቢሉህ አቤት
የምትል ነህና የሁሉ ባለቤት
ሰቆቃችን አይተህ ጩኸታችን ሰምተህ
ደንታ የሌለውን ድንጊያውን አውጥተህ
ለመሪዎቻችን ለሰላሳ ልብ ሰጥተህ
ከጎሰቋላው ኑሮ ከዚህ ከመከራ
መሰስ አርገህ አውጣን ጌታ ሆይ አደራ!

ከዘር፣ ከሀይማኖት፣ ከጎሳ ቆጠራ
ከሥልጣን ሽኩቻ ከጠብ ከአቲካራ
ከሙስና አረንቋ ከጭቆና አቧራ
መሰስ አርገህ እውጣን ጌታ ሆይ እደራ!
እዎ! ጌታ ሆይ እደራ!

ከእዴኛው ወርቁ